በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦክቶበር 1-10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም ከኦክቶበር 11-20 እና ከኦክቶበር 21-31 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2024

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ....- 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 4 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ....- 4 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....- 4 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....- 5 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 5 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 6 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 6 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ....- 7 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ....- 8 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ....- 9 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 9 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 10 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 10 -




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ


ባለፉት አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከቀን ወደ ቀን እየተስፋፉ ከመምጣታቸው ጋር በተያያዘ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ እንዲሁም በክረምት ወቅት ዝናብ ሲያገኙ የነበሩትን የሀገሪቱ አከባቢዎችን ጨምሮ ዝናብ ማግኘታቸውን ቀጥለው ተስተውለዋል፡፡ በመሆኑም፤ በዚህ ወቅት ዝናብ በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙት የደቡብ ኦሮሚያና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ዝናብ ያገኙ ቢሆንም፤ የደቡብ ሶማሌ አካባቢ ግን በጥቂት ቦታ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ጠንከር ያለ የደመና ክምችት ተስተውሎባቸዋል። በተጨማሪም የዝናቡ ሥርጭት ወደ ሰሜን ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ መካከለኛው፣ ሰሜን ምሥራቅና ምሥራቅ ኢትዮጵያ ከመስፋፋቱም ባሻገር አንዳንድ አካባቢዎችም በፀሐይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ጠንካራና ዝናብ ሰጪ ደመናዎች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። ከባድ ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከል በአቦቦ 32.6 እና 30.8፣ በሀሮማያ 33.0፣ በአልጌ 66.0 እና 35.0፣ በአንገር ጉቲን 45.6 እና 33.2፣ በአሶሳ 32.2 እና 39.4፣ በአዋሽአርባ 40.0፣ በበደሌ 33.7፣ በቡለን 30.2 እና 30.4፣ በቡኢ 30.5፣ በቡሬ 67.5፣ በጭፍራ 40.0፣ በጭራ 30.2፣ በዱብቲ 51.2፣ በዳሊፋጊ 34.5፣ በእነዋሪ 38.5፣ በፉኚዶ 73.6፣ በጋምቤላ 38.0፣ በገለምሶ 36.2፣ በጊኒር 75.6 እና 34.0፣ በሀረር 52.0፣ በጃራ 30.4፣ በማጂ 84.3፣ በማንኩሽ 33.5፣ 52.0 እና 84.6፣ በማሻ 44.5፣ በመተማ 39.3፣ በሞያሌ 46.0፣ በፓዌ 45.4 እና 47.2፣ በሳውላ 30.3 እና 37.5፣ በሽርቆሌ 36.2፣ በሾላ ገበያ 43.3፣ በቁልቢ 36.9፣ በጉብሬ 46.2፣ በካራሚሌ 34.0፣ በአለም ተፈሪ 39.2፣ በግራዋ 35.7፣ በአዋሮ 34.0 በጉሊና 45.0፣ በጠርጫ 32.2 እንዲሁም በወራቤ 33.1 በሚ.ሜ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት ቀናት በ38 የተለያዩ የሀገሪቱ ጣቢያዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የሀገሪቱ ጣቢያዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40-84.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካካል በአልጌ፣ በአንገር ጉቲን፣ በአዋሽአርባ፣ በቡሬ፣ በጭፍራ፣ በባቲ፣ በጊኒር፣ በሀረር፣ በማጂ፣ በማንኩሽ፣ በማሻ፣ በሞያሌ፣ በፓዌ፣ በጉብሬ እንዲሁም በጉሊና ይጠቀሳሉ (ምስል 1)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

1-10 ኦክቶበር 2024 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ የዝና መጠን




ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም እና የደቡብና ሰሜን ወሎ፣ ዋግህምራ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል የማሂ፣ ሃሪ፣ ፈንቲ እና ጋቢ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሃረርጌ ዞኖች፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ እንዲሁም ቦረናና ምስራቅ ቦረና፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ እና የየም ልዩ ዞን እና ሀላባ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከሶማሌ የሊበን፣ የዳዋ የሲቲና ፋፈን ዞኖች፤ አዲስ አበባ እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ ላይ ከ16-178 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ3-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም ከትግራይ የመካከለኛው፣ የምስራቅና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ እና አውሲ ዞኖች እንዲሁም ከሶማሌ የኤረር፣ ነጎብ፣ ጃረር የቆራሄ፣




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

የሸበል፣ የዶሎ እና የአፍዴር ዞኖች ላይ ከ6-15 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ3 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ አዊ እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቦረና እና ጉጂ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ደቡብ ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ሰሜን ምዕራብ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ ካማሺ፣ አሶሳ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ አኝዋክ፣ ኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ እና ጠምባሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አማሮ፣ ኣሪ፣ ባስኬቶ፣ ቡርጂ፣ ደራሼ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ፣ ኮንሶ፣ ደቡብ ኦሞ እና ወላይታ ዞኖች፣ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በሰሜን ምሥራቅና በምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተገኘው በመጠንም ሆነ በስርጭት የተስፋፋ ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲሻሻል አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚኙት እንደ ማሽላና በቆሎ ላሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ፍሬ በማፍራትና በማበብ ላይ ለሆኑት የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተገኘው እርጥበት ጥምር ግብርና ለሚያከናውኑ የበደቡብ ኦሮሚያ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወንም ሆነ ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። እንዲሁም በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ ቆላማው አካባቢ ለሚኖሩ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች በቂ የግጦሽ ሣርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ-ሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ኦክቶበር የመጀመርያዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ አዋሽ፣ መካከለኛው እና ታችኛው ተከዜ፣ የላይኛዉ እና የመካከለኛው ዋቤ ሸበሌ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ለገፀ ምድርና ለከርሰ ምድር ውሃ ሃብት መጎልበት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ወደ ግድቦች የሚገባውን የውኃ ፍሰት በመጨመር የመስኖ ሆነ የሀይል ማመንጫ ግድቦች በቂ እና በመጪው ደረቅ የበጋ ወራት የተሻለ የውኃ አቅርቦት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም በአፋር ደናክል፣ በኦጋዴን እና በምራባዊ ታችኛው ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ መጠንኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ማለትም አብዛኛው አፋር ደናክል፣ ኦጋዴን፣ ታችኛው ዋቤ ሸበሌ፣ በጥቂት ታችኛው አዋሽ እና ጥቂት ላይኛው ተከዜ ደረቅ ሁኔታ ስር እንደነበሩ የተተነተኑ የውኃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥሉት የኦክቶበር ሁለተኛዉ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረናና ጉጂ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅትን ዝናብ እያገኙ በነበሩት በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ዝናብ ቀጣይነት ይኖረዋል (ካርታ 6)፡፡ እንዲሁም በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ጋር ተያይዞ በምዕራብና ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፤ ከፋ፣ ሸካና ማጂ አከባቢዎች ላይ በጥቂት ስፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡


በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ፣ ወላይታ፣ ኮንሶ፣ አማሮ፣ ባስኬቶ፣ ቡርጂ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ፋፋን፣ ኤረር፣ ጀረር፣ ኖጎብ፣ ሊበን፣ ቆራሂ ዶሎ፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር እና ሸበል ዞኖች፤ እንዲሁም ሀረሪ እና ድሬዳዋ ላይ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ እንዲሁም ከክረምት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ ባሉት አከባቢዎች ማለትም ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ ወለጋ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡

በሌላ በኩል ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ከአማራ ክልል ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ጎጃም፣ አዊ ዞኖች እና ባህርዳር ዙሪያ፤ ከትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ እና የምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የደቡብ እና የማዕከላዊ ጎንድር ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ከአማራ ክልል በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፤ ሰሜን ሸዋ፣ እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል የደቡብና የደቡብ ምስራቅና ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ፋንቲ፤ ማሂ፣ ሃሪ፣ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ) ፤ አዲስ አበባ፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6) ፡፡





ካርታ 6 ኢ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥሉት የኦክቶበር ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተመሳሰይ ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም በጸሀይ ኃይል ታግዘው ከሚፈጠሩ ጠንካራ ደመናዎች በተለይም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋና ሰፊ ቦታዎችን የሸፈነ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ይኖራል (ካርታ 7) ፡፡




ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ አስር ቀናት በተለይም በደቡብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጠበቀው የተሻለ እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ እንዲሁም ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የተሟላ ዕድገት የሚያስፈልጋቸውን እርጥበት ከማሟላት አንፃር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት እና ጥምር ግብርና በሚያከናውኑ የቦረና እና የጉጂ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወንም ሆነ ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚፈጠረው እርጥበት ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። የውኃ አጠር በሆኑ የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚጠበቀው እርጥበት ሁኔታ የዝናብ ውኃን ለመሰብሰብና ለማከማችት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በአንጻሩ በአንዳንድ የምስራቅ ሸዋ፣ አርሲ፣ ምዕራብ ሸዋ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሀረርጌ እንድሁም በሰሜንና ደቡብ ወሎ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በተለይም በደረሱ እና በመሰብሰብ ላይ በሚገኙ እንደ ሰሊጥ፣ ጤፍ እና ስንዴ በመሳሰሉ ሰብሎች ላይ አሉታዊ ጎን ሊኖረው ስለሚችል አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው አካላት በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ ለመሰብሰብ የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ከወዲሁ ማድረግ ያስፈልጋል።

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ ቀናት በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ የታችኛውና የመካከለኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ እና የስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሚደርስ የእርጥበት መጠን ያገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ የገፀ ምድር የውሀ ሀብትን ከማጎልበት አንጻር የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም የመስኖም ሆነ የሀይል ማመንጫ ግድቦችን በመጪው የበጋ ደረቅ ወራት አስተማማኝና በቂ የውኃ አቅርቦት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ጎን ይኖረዋል። በሌላ መልኩ የታችኛውና የመካከለኛው ዋቤ ሸበሌ እና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች በአንጻሩ መጠነኛ እርጥበት የሚኖራቸው ሲሆን፤ የሚገኘውን የዝናብ ውሀ ለማሰባሰብ እና ለማጠራቀም የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ማከናወን ያስፈልጋል።



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et